የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን

# JERUSALEM EVANGELICAL CHURCH

## መሠረተ ዕምነትና መተዳደሪያ ደንብ

# ማውጫ


| | | ገጽ |
|---|---|---|
| አንቀጽ-1 | ስም | 1 |
| -2 | ግንኙነት | 1 |
| -3 | መሠረታዊ እምነት | 1-5 |
| -4 | የክርስትና ሥርዓቶች ( ቅዱሳት ሚሥጥራት ) | 5-7 |
| -5 | ክርስቲያናዊ ሥነምግባር | 7 |
| -6 | አባላት | 7-9 |
| -7 | በአባላት ላይ ስለሚፈጸሙት ሥ ሥርዓቶች | 9-10 |
| | *ከአንቀጽ-8-16 የቤ/ክ አገልጋዮች* | 10-16 |
| -8 | መጋቢ | 10 |
| -9 | ሊቀመንበር | 10 |
| -10 | ሽማግሌዎች | 11 |
| -11 | የሽማግሌዎች ሥርዓተ ምርጫ | 11-12 |
| -12 | የሽማግሌዎች ተግባር | 12-13 |
| -13 | ምክትል ሊቀመንበር | 13 |
| -14 | ጸሐፊ | 13 |
| -15 | ሂሳብ ሹም | 13 |
| -16 | ኦዲተር | 13 |
| -17 | ገንዘብ ያዥ ( ግምጃ ቤት) | 13-14 |
| -18 | ወንጌላዊ | 14 |
| -19 | ዲያቆናት- ሥርዓተ ሹመት | 14-15 |
| - 20 | ኮሚቴዎች | 16 |

# የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን መሠረተ እምነትና መተዳደሪያ ደንብ ።

## አንቀጽ አንድ

1– ስም፦ በዚህ መሠረተ ዕምነትናመተዳደሪያ ደንብ መሠረት የተቋቋመችው ቤተክርስቲያን የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን በስዊድን ተብላ ትጠራለች ። ዋናው ጽ/ቤት በስቶክሆልም ይሆናል።

## አንቀጽ ሁለት

2–ግንኙነት፦ የኢ.ወ.ቤ.ክ በእምነትና በዓላማ ከሚመሳሰሉአት አብያተክርስቲያናትና ሕብረቶች ጋር የቅርብ ግንኙነት ታደርጋለች።

## አንቀጽ ሦስት

## መሠረታዊ ዕምነት

3:1– እግዚአብሔር፦ ሁሉን ፈጣሪ , ሁሉን ቻይ, ታላቅ , የማይወሰን, ቅን ፈራጅ, ዘልዓለማዊና ፍጹም የማይለወጥ, ራሱን በሦስት የገለጸው, ይኸውም በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በአንድ አምላክ ታምናለች።

| | | |
|---|---|---|
| ዘዳ. 6 ÷ 4–5 | መዝ.(139) ÷ 7–12 | ሚልክ.3 ÷ 6 |
| መዝ.90 ÷ 2 | መዝ.147 ÷ 5 | ዮሐ.17 ÷ 11 |
| ኢሳ. 40 ÷ 28 | ማቴ. 28 ÷ 19–20 | ዘፍ. 1÷ 26 |

3.2 – እግዚአብሔር አብ፦ እግዚአብሔር አብ በፍቅሩና በምሕረቱ በአብርሃም በኩል ለሰብአዊ ፍጡር ሁሉ በገባው ቃልኪዳን መሰረት የሰጠውን የተስፋ ቃል በመጠበቅ ለሰው ልጆች ሁሉ በ ልጁ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ደህንነት እንዳዘጋጀ ልጁንም አምነው ተቀብለው ኃጢያታቸውን ለሚናዘዙ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣን እንደሰጠ ታምናለች።

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ.17 ÷ 1–2 | ኢሳ. 63 ÷ 16 | ኤፌ. 4 ÷ 6 |
| ዘጸ:6 ÷ 25 | 1ቆሮ. 8 ÷ 6 | ዮሐ. 1 ÷ 12 |

3.3– እግዚአብሔር ወልድ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር አብ ዘልዓለማዊ ልጅ መሆኑን ፡ ከመንፈስ ቅዱስ ተጸንሶ ከድንግል ማርያም

መወለዱን ፡ ፍጹም ሰውና ፍጹም አምላክ ሆኖ በመገለጥ ኃጢአት ያልሰራ ነገር ግን የኃጢአተኞች ምትክ ሆኖ በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ፡ ደሙን በማፍሰስ ሞቶ ለሰው ልጅ ኃጢአት በቂ ቤዛ አድርጎ ሰውን በመዋጀት ከእግዚአብሔር ጋር ማስታረቁን ፡ ወደ ሲኦል መውረዱን ፡ ከሞት ተነስቶ
በክብር ማረጉን ፡ ለሰው ልጅ ሊያማልድ ዘወትር በአባቱ ቀኝ በሕይወት መኖሩን ፡ የቤተክርስቲያን መሥራቿና ራስ መሆኑን ፡ ለፍርድ ዳግመኛ የሚመለስ መሆኑን ታምናለች ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዘፍ. 1 ÷ 2 | ሐ.ሥራ 16 ÷ 31 | ዕብ. 13 ÷ 18 | ዕብ. 1 ÷ 8 |
| ፩ኛ.ጢሞ.3 ÷ 16 | የሐ. 1 ÷ 12 | የሐ.1 ÷ 1–14,18 | ዕብ. 7 ÷ 25 |
| ዕብ. 4 ÷ 15 | ማቴ. 25 ÷ 31–41 | | |

3.4– *እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ፦* መንፈስ ቅዱስ ከአብና ከወልድ የተላከ፣የሚሰርጽ ፡ መንፈሳዊ ምልአተ አካል ያለው መለኮት መሆኑን፣ ሕይወትን የሚሰጥ ፡ ዓለምን ስለኃጢአት ፡ ስለጽድቅና ስለፍርድ እንደሚወቅስ ፡ በአማኞች ውስጥ አድሮ ወደ እውነት ሁሉ እንደሚመራቸው፣ የቅድስናን ኑሮ ለመኖር እንደሚያስችላቸውና ለአገልግሎትም ኃይልንና የጸጋ ሥጦታዎችን እንደሚሰጣቸው ታምናለች ።

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ.1÷2 | ፩ኛ ቆሮ.12÷4–11 | የሐ.16÷7,8,13 |
| ማቴ.3÷16 | ሐ.ሥራ 1÷18 | ሐ.ሥራ 5÷3–4 |
| ሮሜ 8÷1–14 | የሐ. 14÷15–16,26 | ፩ኛ ቆሮ. 3÷16 |
| ሕዝ. 37÷ 14 | | |

3.5 *መጽሐፍ ቅዱስ፦* መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል መሆኑን ፡ ብሉይና አዲስ ኪዳን ተብሎ በመጠራት ብሉይ 39 መጻሕፍት አዲስ 27 መጻሕፍት በጠቅላላው 66 መጻሕፍት ብቻ መሆኑን ፡ እንዲሁም ቅዱሳን ሰዎች በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት የጻፉት ሊታመንበት የሚገባ ዘለዓለማዊና የማያልፍ ሥልጣን ያለው የቤተክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረቱ እርሱ ብቻ መሆኑን ታምናለች ።

| | | |
|---|---|---|
| ፪ኛ ሳሙ. 23 ÷ 2 | ማቴ.5÷ 18 | መዝ.(12)÷ 6 |
| ማቴ.24 ÷35 | መዝ.(119)÷108 | ፪ኛ ጢሞ 3 ÷16–17 |
| ፪ኛ ጴጥ. 1÷ 20–21 | ራዕይ 22÷ 18 | ዕብ. 4 ÷12 |

3.6 *ሰይጣን፦* ሰይጣን በውበቱና በጥበቡ ታብዮ በእግዚአብሔር መንግሥትና እቅድ ላይ ያመጸ ፡ በማመጹም በእግዚአብሔር ወደታች የተጣለ ፡ ርኩስ መንፈስ ፡ የኃጢአትና የጥፋት ሁሉ ምንጭ ፡ የእግዚአብሔርና የሰው ጠላት ፡ ነፍሰ ገዳይ ፡ የዚህ ዓለም የጨለማ ገዢ ፡ ሐሰተኛና የሐሰት አባት ፡
በመጨረሻም ከተከታዮቹ ጋር ወደተዘጋጀለት ወደ ገሃነመእሳት የሚጣል መሆኑን ታምናለች ።

| | | |
|---|---|---|
| ዘፍ.3÷ 1–5 | ፩ኛጴጥ.5÷ 8 | ኢሳ.14÷ 12–15 |
| ራዕይ2÷ 10 | የሐ.8÷ 44 | ፪ኛቆሮ.11÷ 14 |
| ሕዝ.28÷ 2.13–15 | ራዕይ 20÷ 10 | |

3.7 *የሰው አፈጣጠርና ውድቀት*፦ ሰው በእግዚአብሔር መልክና ምሳሌ መፈጠሩን ፡ ሥልጣንና ትዕዛዝ መቀበሉን

፡ ሰው ግን የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ በመጣሱ በመንፈሳዊ ረገድ የሞተ ኃጢአተኛ መሆኑን ፡ የእግዚአብ– ሄር ክብር የጎደለው ከሥጋዊ ሞትና ከሠይጣን በታች መሆኑን ፡ ከዚህ ውድቀት ራሱን ለማዳን አለመቻሉን ታምናለች ።

ዘፍ. 1÷26–27
ዘፍ. 3÷1–17
ሮሜ 3÷23 ዘፍ 2÷7
ኤፌ.2÷1–3

3.8 *የዘላለም ደህንነት*፦ ሰው ኢየሱስ ክርስቶስ በፈጸመው ሥራ በማመን ፡ በጸጋ ብቻ እንደሚድንና እንደሚጸድቅ ዳግመኛ ከውኃና ከመንፈስ በመወለድ የእግዚአብሔር ልጅ እንደሚሆን በክርስቶስ መንፈሳዊ በረከትና የዘላለም ሕይወትን እንደሚያገኝ ታምናለች ።

ዮሐ 1÷12–13
ዮሐ 3 ÷36
ሐ.ሥራ 13 ÷38–39
ዮሐ 3 ÷5–6
ሮሜ 3 ÷20–26
፩ኛዮሐ. 5÷11
ዮሐ 3÷8, 16
ኤፌ. 2÷ 8–9

3.9 *መለየት* ፦ አማኞች ከአለማዊነትና በዓለም ከሚገኙ ከንቱ ነገሮች ተለይተው ለእግዚአብሔር ክብር በኢየሱስ ክርስቶስ የጽድቅ ኑሮ መኖር እንደሚገባቸው ታምናለች

ሮሜ12 ÷12
፩ኛ ጴጥ.2÷9
፪ኛቆሮ. 6÷14–18
ዮሐ. 16÷15
ቲቶ 2÷11–14

3.10 *አንድነት* ፦ የክርስቶስ አካል የሆኑት እውነተኛ አማኞች ሁሉ በመንፈስ አንድነት እንዲኖራቸው ታምናለች ።

ሮሜ 12÷5
፩ኛ ቆሮ. 12÷13–26
ኤፌ.4÷1–6

3.11 *ትንሣኤ ሙታን* ፦ ኢየሱስ ክርስቶስ ከሞት እንደተነሳ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ ተመልሶ ሲመጣ ጻድቃንና ኃጥአን ከሞት እንደሚነሱ ጻድቃን ወደ ዘላለም ሕይወት ደስታ ኃጥአን ግን ወደ ዘላለም ቅጣትና ስቃይ እንደሚሄዱ ታምናለች ።

ዮሐ. 5÷28–29
ማቴ.25 ÷46
፩ኛቆሮ. 15÷ 20–23 , 42–44
ራዕይ 20÷13

3.12 *ገነትና ሲኦል* ፦ በሞትና በሲኦል መካከል ባለው ጊዜ ጻድቃን ከክርስቶስ ጋር በገነት በደስታ ፡ ኃጥአን ግን በሲኦል በመሰቃየት እንደሚኖሩ ታምናለች ።

ሉቃስ 16÷19–31 ሉቃስ 23÷43 ፊሊጵ.1÷23 ማቴ.11÷23–24

3.13 **የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት**፦ የክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የአማኞች ሁሉ ተስፋ መሆኑን በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት ጊዜም በሕይወት ያሉና ከሙታንም የሚነሱ አማኞች ጌታን በአየር እንደሚቀበሉት ከዚያ በኋላም በዘላለም ደስታ ከእርሱ ጋር እንደሚኖሩ ታምናለች ።

ማቴ. 24÷30–31, 44
፩ኛ ተሰ.4÷13–18
ማቴ. 25÷31
፩ኛዮሐ.2÷28
ሐ.ሥራ.1÷11

3.14 **መንግሥተ ሰማያትና ገሃነመ እሣት**፦ መንግሥተ ሰማያት አማኞች ለዘላለም በደስታ የሚኖሩበት ሥፍራ መሆኑን ፡ ገሃነም እሳት ደግሞ ለዲያብሎስና ለተከታዮቹ የተዘጋጀ ከእነርሱም ጋር የማያምኑ አብረው የሚሰቃዩበት ዘልዓለማዊ የስቃይ ቦታ መሆኑን ታምናለች ።

ማቴ.25÷34 , 41–46
ራዕይ 22÷1–5
ይሁዳ ቁጥር 7
ራዕይ 20÷10–15
ራዕይ 21÷1–7 , 10–11

3.15 **ቤተክርስቲያን**፦

ሀ.የቤ/ክ መሠረትና መሥራች ራስና መሪ ጌታ ኢየሱስ እንደሆነ ታምናለች ።

ማቴ. 16÷18
ዕብ. 3÷1
ኤፌ. 2÷20–22
ኤፌ. 5÷23–24
፩ኛጴጥ.2÷7–9
፩ኛቆሮ. 3÷11
ቆላስ.1÷18

ለ. **ቤተክርስቲያን**፦ ክርስቶስን በማመን ንስሃ ገብተው ዳግመኛ የተወለዱና በአንድ መንፈስ የተጠመቁ አማኞች ሁሉ ያሉባት የክርስቶስ አካል መሆንዋን ፡ ለእግዚአብሔር ቃል መታዘዝ እንዳለባት ታምናለች ።

ማቴ. 16÷18
ኤፌ. 1÷22–23
ሐ.ሥራ 16÷4–5
፩ኛ ቆሮ. 12÷12–27
ገላ. 3÷26–27
ቆላ. 1÷18

3.16 **የቤተክርስቲያን ሥልጣንና አገልግሎት**፦ በመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት መሠረት ጌታ ለቤተክርስቲያን ከዚህ የሚከተሉትን ሥልጣንና ኃላፊነት እንደሰጣት ታምናለች ።

ሀ. ሥራዋን እንደሚገባ አደራጅታ በወንጌል ሰዎችን መጥራት እንዳለባት ታምናለች ።

ማቴ. 28÷20
ማር. 16÷15

ለ . አማኞችን መምከር , ማስተማርና መገሰጽ እንዲሁም ወደ መንፈሳዊ ኑሮ መምራት ።

ማቴ.18÷15-18 ገላ.6-1-2 1ኛ ጢሞ.5÷20
ቲቶ 2÷15 ቆላ.1÷28

ሐ . የቤተክርስቲያን አገልጋዮችን መሾም ።

መ.ሥራ. 6÷1-6 ሐ.ሥራ 13÷1-3 ሐ ሥራ 14÷23

ሠ. የሰውን መንፈስ, ነፍሱንና ሥጋውን መመገብ ።

ገላ. 2÷10 ሐ ሥራ 6÷1-6 ሮሜ ÷ 15÷26-27
1ኛ ጢሞ.4÷6 ማቴ. 25÷35-36 ፪ቆሮ 8÷13-15
ያዕ. 2÷14-17

ረ- ቤ/ክ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበለችውን አደራ ዓላማዋ አድርጋ በወንጌል መሪነት ለፍትህ ትቆማለች ።

ኢሳ. 1÷16-17 ፩ሳሙ. 12÷3-4 ሉቃስ 3÷19-20

## አንቀጽ አራት

## 4. የክርስትና ሥርዓቶች ( ቅዱሳት ምሥጢራት ):-

ቅዱሳት ምሥጢራት የሚባሉት በሚታይና በሚጨበጥ መንገድ መንፈሳዊ ምሥጢርን የሚገልጡ ጌታ ኢየሱስ በዚህ ምድር ሳለ የፈጸማቸውና እንድንፈጽማቸውም ያዘዘን፣ በጌታ በኢየሱስ ሕይወት ውስጥ ትርጉምና መንፈሳዊ ምሥጢርን ያዘሉና ብናደርጋቸውም በረከትን የሚያስገኙ መሆናቸውን ታምናለች ።

### 4.1 የአማኝ ጥምቀት :-

ሀ. ሰው ንስሃ ገብቶ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በእምነት አዳኙና ጌታው አድርጎ ሲቀበል ለውሃ ጥምቀት የተዘጋጀ ይሆናል ።

ማቴ. 3÷13-17 ማቴ. 28÷19-20 ሐ.ሥራ 10÷44-48
ሐ.ሥራ 2÷38 ሐ.ሥራ 8÷36-39 ቆላ. 2÷12
ሮሜ. 6÷1-6 ሐ.ሥራ 16÷30-34

ለ. አንድ አማኝ ከመጠመቁ በፊት የመሠረተ ዕምነት ትምህርትና የኃይማኖትን ነገር ሁሉ መማር አለበት ።

ሐ. በጌታ በኢየሱስ ያለውን እምነት በሕዝብ ፊት ገልጾ አዲስ ሆኖ መወለዱን አረጋግጦ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ በአንድ አምላክ ስም የተጠመቀ መሆን አለበት ።

መ. አማኙ ከተጠመቀ በኋላ የጌታ እራት ( ቅዱስ ቁርባን ) ይቀበላል ። ከዚያም የቤተክርስቲያን አባል ይሆናል ።

4.2 ***የጌታ እራት ( ቅዱስ ቁርባን )*** የጌታ እራት የጌታ ሞት መታሰቢያ ስለሆነ መሳተፍ የሚገባቸው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኛቸውም አድርገው የተቀበሉ ፡ ከጌታ ጋር ሕብረት እንዳላቸው በጥምቀት የመሠከሩና በቅጣት ላይ ያልሆኑ ናቸው ።

ሉቃስ 22÷19–20 1ቆሮ. 10÷16–17 1ቆሮ.11÷23–28

## 4.3 ***ጋብቻ***

ሀ. ጋብቻ በእግዚአብሔር ቃል መሠረት በአንድ ወንድና በአንዲት ሴት መካከል የሚፈጸም እግዚአብሔር የመሠረተውና የቀደሰው የሁለት አማኞች አንድነት ሲሆን ሞት ብቻ ኪዳኑን የሚለየው ፡ እንዲሁም ቤተክርስቲያን ልትንከባከበውና ልትጠብቀው የሚገባ ቅዱስ ሥርዓት መሆኑን ታምናለች ።

ዘፍ. 2÷18–25 ማር. 10÷2–12 ማቴ.19÷3–9 ኤፌ.5÷23–33
፩ቆሮ 7÷39 ፩ቆሮ 7÷10–16 ዕብ.13÷4

ለ.የእግዚአብሔርን ቃል የማይከተልና መንፈሳዊ አቋሙ ያልተመሠከረለት ክርስቲያን በቤተክርስቲያን ሊያገባ አይችልም ።

ሐ. ለጋብቻ ያልተፈቀቀዱትን ሴትና ወንድ እንዲጋቡ ማስገደድ ክልክል ነው ።

መ. ክርስቲያኑ ወይም ክርስቲያኗ ያላመነችውን ወይም ያላመነውን እንዲያገቡ አይፈቀድም ። ከዚህም በቀር ማንኛውም አባል ካላመነች ወይም ካላመነው ጋር መተጫጨት አይገባቸውም ።

2ቆሮ. 6÷14

ሠ. ያላመነ ባል ወይም ያላመነች ሚስት ያለው አማኝ ግን አብረው መኖር ከወደዱ አይተዋት ወይም አትተወው ።

1ቆሮ. 7÷12–13

4.4 ***ልጆችን ለጌታ አደራ መሥጠት፦*** ልጆችን ለጌታ አደራ መሥጠት በብሉይ ኪዳን ከእግዚአብሔር ለሕዝቡ ለእሥራኤል ተሰጥቶ ፡ በአዲስ ኪዳን በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ እርሱም ራሱ ባገልግሎቱ ጊዜ በተግባር ሲገልጸው የነበረና ቤተ ክርስቲያንም ከአማኝ ወላጅ ለተወለዱ ሕጻናት የምታከናውነው ሥርዓት ነው ። ይህም ሥርዓት በእግዚአብሔር ባርኮትና ጥበቃ ሕጻናትን ለጌታ አሳልፈን የምንሰጥበትና ወላጆችም እግዚአብሔርን በማመስገን በጌታ መንገድና ሥርዓት ሕጻናት ልጆቻቸውን ለማሳደግ ቃል የሚገቡበት መሆኑን ታምናለች ።

ልቃስ 2÷25–32 ዘፍ.18÷17–19

4.5 **የቀብር ሥነ ሥርዓት** :- አንድ አማኝ ከዚህ ዓለም በሞት ተለይቶ ወደ ጌታ ሲሄድ ቤ/ክ የእግዚአብሔርን ቃል ላላመኑ ሁሉ በማስተማርና በመምከር

ለቤተሰብና ለወገኖች ሁሉ የማጽናኛ ቃልን በማካፈል የቀብር ሥነ ሥርዓት ትፈጽማለች ።

ሐ.ሥራ 8 ÷2መክ. 7÷2 ቲ.27 ÷ 57–61 ሮሜ12÷15

## አንቀጽ አምስት

### 5.1 ክርስቲያናዊ ሥነ ምግባር

ሀ. ማንኛውም ክርስቲያን ከሁሉም በላይ በቅድሚያ እግዚአብሔርን መፍራት ፡ ማፍቀርና በመታዘዝም ማክበር እንደሚገባው ታምናለች ።

ምሳሌ 1÷7 ማቴ. 22÷37
ሐ ሥራ 4÷18–20 ሐሥራ 5÷29

ለ. በተቻለ መጠን ከሰው ጋር በሰላምና በፍቅር መኖር እንዳለበት ታምናለች ።

ሮሜ 12÷10–21 ዘፍ. 14÷21 ዘፍ.19÷17–18

ሐ. ቤ/ክንና የቤ/ክ መሪዎችን ( አገልጋዮችን ) በእግዚአብሔር ቃል መሠረት ሊያከብራቸው ሊያፈቅራቸውና ሊታዘዛቸው እንደሚገባ ታምናለች።

፩ተሰ.5÷12–13 እብ.13÷17 ፩ጢሞ. 5÷17

መ. ክርስቲያን ለዓለም ለብርና ለጥቅም ሳይሸነፍ በኑሮውና ከእግዚአብሔር በተሰጠው ማንኛውም ነገር ባለአደራነቱን ሳይዘነጋ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማስቀደም እንደሚገባው ታምናለች ።

ሮሜ 12÷1–2 ፩ኛ ዮሐ. 2÷ 1–6 , 15–17

ሠ. ክርስቲያን እግዚአብሔር ከሰጠው በረከት ሁሉ አሥራትና በኩራትን ለእግዚአብሔር ቤት ሥራ ለቤተክርስቲያን መስጠት እንዳለበት ታምናለች ።

ምሳሌ 3÷9–10 ሚልክ. 3÷7–12 ዘዳ 16÷16
ዘዳ. 14÷22 ማር. 12÷17 ማቴ 23÷ 23

## አንቀጽ ስድስት

### 6. አባላት

## 6.1 አባላት የሚሆኑት

ሀ. ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን የግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ ( ዳግመኛ የተወለደ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን ለመታዘዝ የወሰነ ) በሦስተኛው አንቀጽ ውስጥ የተዘረዘሩትን መሠረታዊ ዕምነቶችንና መተዳደሪያ ደንቡን በሙሉ የተቀበለ አማኝ የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን አባል ይሆናል ።

ለ. ከሌላ ሥፍራ የመጣ አንድ ማኅበረ ምዕመን ይህን የቤ/ክ መሠረተ ዕምነትና መተዳደሪያ ደንብ በሙሉ የተቀበለ ለቤ/ክኒቱ ሽማግሌዎች አመልክቶ የሽማግሌዎች ጉባኤ ከተቀበለው የኢ.ወ.ቤ/ክ አባል ይሆናል ።

ሐ. አንድ አጥቢያ ቤ/ክ ወይም ሕብረት ባለችበት ሥፍራ ሆና የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን አባል ለመሆን ብትጠይቅ በ6.1 ለ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ አባል ትሆናለች ።

መ. ከሌላ ሥፍራ በጊዜያዊነት ወይም በቋሚነት ለመኖር የመጣና የሌላ ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን አባል የሆነ በኢየሩሳሌም ቤ/ክ በተከታታይ የሚያመልክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን የግል አዳኙ አድርጎ የተቀበለ አማኝ የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን ተባባሪ አባል ይሆናል ። ይህም የሚሆነው የኢየሩሳሌም ወ/ቤ.ክ መሠረተ እምነት የተቀበለና ከቤ/ክኒቱ መተዳደሪያ ደንብ ውጪ የማያስተምር ሊሆን ይገባዋል ። ሆኖም ተባባሪ አባል ለመሆን ጠይቆ ቤ/ክኒቱ የተቀበለችው እንደሆነ ብቻ ነው ።

ሠ. ተባባሪ አባላት በአስተዳደርና በቋሚ ወንጌላዊነት ማገልገል የማይችሉ ሲሆን በአንጻሩ ግን በመተዳደሪያ ደን ላይ የተጠቀሰው የአባላት መብትና ግዴታ በሙሉ ይመለከታቸዋል ።

## 6.2 የአባላት ሥራና ሁኔታ ፦

ሀ. የቤ/ክኒቱን መተዳደሪያ ደንብ መታዘዝ አለባቸው ። ዓላማቸውም ነፍሳትን ወደ ክርስቶስ መመለስ መሆኑን ማወቅ አለባቸው ።

ለ. የቤ/ክኒቱ አባሎች በቤተ/ክኒቱ ፕሮግራሞች ላይ መገኘት ይገባቸዋል ።

ሐ. ምዕመናኑ የሚሰበሰቡበት ወይም የሚገኙበት ምክንያቶች ፡

– እግዚአብሔርን በእውነትና በመንፈስ ለማምለክ ። ዮሐ. 4÷24

– ለመንፈሳዊ ትምህርትና ለአገልግሎት ።

ሐዋ.2÷42 ኤፌ. 4÷11–13

– ስለሃገር ሰላምና ሰዎች ሁሉ እንዲድኑና እውነቱንም ወደ ማወቅ ለመድረስ እንዲችሉ ለመጸለይ ።

– በአዲስ ኪዳን እንደታዘዘው የጥምቀትንና የጌታን ዕራት ለመፈጸም ። 1ኛ.ቆሮ. 11÷23–34

## አንቀጽ ሰባት

## 7 . በአባላት ላይ የሚፈጸሙ የሥነሥርዓት እርምጃዎች :

### 7.1 ወደ ልዩ ልዩ የሥ , ሥ , እርምጃዎች የሚያደርሱ ሁኔታዎች፦

ሀ. በወንድሞችና በእህትሞች መካከል ለሚደረገው መበዳደል በእግዚአብሔር ቃል መሠረት እርምጃ ይወሰዳል ።

ማቴ. 5÷23–24 ማቴ. 18÷15–18 ፩ቆሮ. 6÷1–6

ለ. በዚህ መሠረታዊ ዕምነትና መተዳደሪያ ደንብ ላይ የመለያየት መንፈስ የሚያመጣ አባል በዚህ ስህተቱ ተገስጾ የማይመለስና ወይም የተቀበለ ሙስሉ በስህተቱ የሚቀጥል ቢሆን ከአባልነቱ ይወገዳል ።

ቲቶ 3÷10–11

ሐ. ያለ ሥርዓት የሚኖሩትንና መጥፎ ጠባይ ያላቸው አባሉች የጥፋታቸው መጠንና ሁኔታ እየታየ ይገሰጻሉ
የሥነሥርዓት እርምጃም ይወሰድባቸዋል ።

፩ተሰ. 5÷14 ፩ጢሞ. 5÷20
፪ተሰ.3÷14–15 ዘሌ. 19÷17–18

መ.የሚያሰክር መጠጥ የሚጠጡም : ሱስ የሚሆኑና የሚያደክሙ ወይም የሚያፈዙ ቅጠላቅጠልና ሥራሥር የሚጠቀሙ ወይም የሚያቀርቡ የሥነሥርዓት እርምጃ ይወሰድባቸዋል ። ምክንያቱም ትምባሆ ሲጋራና የሚያሰክር መጠጥ ሌሉችም ራስን ለመቆጣጠር የማያስችሉ ሱሶች አባሉችን የሚጎዱና ወደ ኃጢአትም የሚመሩ ስለሆኑ ነው ።

፩ቆሮ. 3÷16–17 ምሳሌ 20÷1 ምሳሌ 23÷20
ምሳሌ 23÷29–35 ፩ቆሮ 6÷19–20 ኤፌ 5÷18

### 7.2 ስለ ምንዝርናና ዝሙት የሥነሥርዓት እርምጃዎች፦

ሀ. አመንዝሮችና ዘማውያን አባሉች ወዲያውኑ ከአገልግሉት እንዲታገዱ ያስፈልጋል ።

ለ. ሥነ ሥርዓት አፍራሽ ሆነው የተቀጡት ወደ አገልግሎታቸው ለመመለስ በመፍቀድ ብቻ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚቀበለውን እውነተኛ ንስሃ ካደረጉ የጥፋታቸውን መጠን እየታየ ጊዜውን ማመዛዘን ይቻላል ።

ሐ. ከቤ/ክ አገልግሎት በዝሙትና በምንዝርና ምክንያት የታገዱት የሥነሥርዓት ቅጣታቸው ጊዜ አልቆ ወደ አገልግሎት ለመመለስ ቢችሉም የኃላፊነት ሥልጣን ለመያዝ የሚችሉት ቢያንስ ቢያንስ ከአንድ አመት በኋላ ሆኖ ያውም በእውነት ንስሃ ገብተው የንስሃ ፍሬ ሲታይባቸውና በመንፈስ ከታደሱ በኋላ ነው ።

መ. ንስሃ ካልገቡ የቅጣታቸው ጊዚያት ምንጊዜም አይወሰንም ።

ሠ. በሥነሥርዓት እርምጃ ላይ የሚገኘው አባል በቅጣቱ ጊዚያት ከቤ/ክኒቱ ማንኛውም አገልግሎት የታገደ መሆኑን ሽማግሌዎች እንደአስፈላጊነቱ ለአባላት መግለጽ አለባቸው ።

ረ. የተወሰነበት የሥነሥርዓት እርምጃ የማይቀበልና በየጊዜውም ጠባዩን እንዲያሻሽል ሲመከር ምክርን የሚንቅ ማንኛውም አባል በጉባኤው መሃል አባልነቱ በግልጽ ይሰረዛል ።

# ከአንቀጽ ስምንት እስከ አንቀጽ ሃያ

## የቤተክርስቲያን አገልጋዮች

## አንቀጽ 8 መጋቢ

ሀ. ከእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮት በአንድ አጥቢያ ቤ/ክ ምዕመናን ለማገልገል ሙሉ ጊዜውን የሰጠ ነው ። ሆኖም ጥሪውን ከሽማግሌዎች 2/3ኛዎች አምነውበት ምዕመናኑም 3/4ኛው የተቀበሉት ሊሆን ይገባል ።

ለ. በወንጌል ትምህርት የሚጸና ፡ በፍቅር ፡ በእምነት ፡ በንጽህና ፡ በቃልና በኑሮ ምሳሌ የሆነ እንዲሁም ለራሱና ለትምህርቱ የሚጠነቀቅ ሊሆን ይገባዋል ።

ሐ. መንጋውን የሚያስተምር ፡ ከስህተት ትምህርት የሚጠብቅ ፡ የሚመክር ፡ የሚመግብ ፡ የሚያጽናና ፡ የሚገስጽና የክርስትናን ሥርዓት የሚያከናውን ይሆናል ።

፩ጢሞ. 4÷11–16 , 5÷ 17 , 6÷11–12
ቲቶ 1÷9–11 , 2÷7–8 ፪ጢሞ. 4 ÷2–5

## አንቀጽ 9 መጋቢ ( ሊቀመንበር )

ሀ. መጋቢው የሽማግሌዎች ጉባዔ ሰብሳቢ ይሆናል ። መጋቢው በሌሌበት የሽማግሌዎች ሰብሰቢ ሊቀመንበሩ ስብሰባውን ይመራል

ለ. የቤተክርስቲያን ጉዳይ ለሽማግሌዎች ውሳኔ ያቀርባል ።

ሐ. በማንኛውም መንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ ከፍተኛ ሥልጣን ይኖረዋል ። በዚህም መሠረት አስፈላጊ ለሆነና አስቸኳይ ሆኖም ሲገኝ ለምክትል ሊቀመንበሩ ወይም ለጸሐፊው ሁለቱም በሌሉ ጊዜ በቅርቡ ለሚገኙ ሽማግሌዎች በማስታወቅ እራሱ ወስኖ እርምጃ መውሰድ ይችላል ። ጊዜ የሚሰጥ ከሆነ ለሽማግሌዎች ጉባዔ በማቅረብ ያስወስናል ።

መ. ማንኛውም መንፈሳዊ አገልግሎት ይቆጣጠራል ፡ ምክር ይሰጣል ፡ በየኮሚቴዎች ስብሰባ ላይ ጊዜው እስከፈቀደለት ድረስ በመገኘት ያበረታታል።

ሠ. መጋቢው ( ሊቀመንበሩ ) ከሽማግሌዎች ጋር በመመካከር አንድ አባል ወደ ሌላ ቤ/ክ ለመዛወር በጽሑፍ ሲጠይቅ የምስክር ወረቀት ይሰጣል ። ከሌላ ቤ/ክ ተዛውረው የምስክር ወረቀት ይዘው የሚመጡትን አስፈላጊውን ማጣራት እያደረገ በአባልነት ይቀበላል ።

ረ. ወደ ቤ/ክ የሚጪመሩትን አባላት የሚሰጠውን መሠረታዊ ትምህርት እንደጪረሱ ብቃታቸውን በመመልከት ከወንጌላዊው ጋር በመሆን ለጥምቀት ያዘጋጃሉ ወይም ያቀያሉ ።

ሰ. ቤተክርስቲያኒቱን በሚመለከቱ ጉዳዮች ቤተክርስቲያኒቱን በመሥራቤቶችና በመሳሰለው ይወክላል ። አፈሳላዊ ደብዳቤዎችንም በፊርማው ወጪ ያደርጋል ።

## *አንቀጽ 10–ሽማግሌዎች*

ሀ. ተጠሪነታቸው ለመጋቢው ይሆናል ።

ለ. በማንኛውም መንፈሳዊ ነክ አገልግሎቶች ላይ ከመጋቢው ጋር በመሆን ውሳኔ ይሰጣሉ ።

ሐ. በማንኛውም የአስተዳደር ጉዳይ ላይ ከመጋቢው ጋር በመሆን ውሳኔ ይሰጣሉ

መ. በማንኛውም የአገልግሎት ቡድን ውስጥ በመገኘት ሊያገለግሉ ይችላሉ ። ሆኖም የሽምግልና መብታቸውን በማንኛውም ውሳኔ ላይ አይጠቀሙበትም ግን እንደማንኛውም አባል መብት አላቸው ።

ሠ. በማያገለግሉበትም የአገልግሎት ክፍል ውስጥ በመገኘት ያበረታታሉ አብረውም ይጸልያሉ ።

ረ. ማንኛውም አስተዳደርና መንፈሳዊ ነክ ነገሮችን በቤ/ክ ውስጥ ይቆጣጠራሉ ።

## አንቀጽ 11.*የሽማግሌዎች ሥርዓተ ምርጫ*

ሀ. ሽማግሌዎች በአስመራጭ ኮሚቴ አማካይነት በጠቅላላ አባላት ድምጽ ብልጫ

ለ.የአስመራጭ ኮሚቴን የሚሰይመው መጋቢውና የሽማግሌዎች ኮሚቴ ይሆናል ፡፡ የአስመራጭ ኮሚቴ ከምዕመናን በጥቆማ የተቀበላቸውን ዕጩዎች መዝኖ ያሳለፋቸውን ለምርጫ ያቀርባል ፡፡

ሐ. የሚመረጡት የሽማግሌዎች ቁጥር ከ ፫ እስከ፯ ይሆናል ፡፡

መ. የሕይወት ምስክርነታቸውና የዕለት ኑሮአቸው በ፩ኛ ጢሞ. 3÷1–7 እና 5÷17–20 ውስጥ እንደተጠቀሰው መሆን ይገባዋል ፡፡ የቤ/ክኒቱን መሠረተ ዕምነትና መተዳደሪያ ደምብ የተቀበሉና የሚፈጽሙ መሆን አለባቸው ፡፡

ሠ. የሽማግሌዎች የአገልግሎት ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል ፡፡ ከሁለት ዓመት አገልግሎቱ በኋላ ግን እንደገና ለምርጫ ሊቀርብ ይችላል ፡፡ ወይም በፈቃዱ ሊተው ይች ላል ፡፡

ረ. የማናቸውም ሽማግሌ ሕይወት በእግዚአብሔር ቃል መሠረት የሚነቀፍ ሆኖ ሲገኝ በመጋቢውና በሽማግሌዎች ውሳኔ ወይም እጅግ ከባድ ከሆነ በጠቅላላው የአባላት ጉባዔ ከአገልግሎቱ እንዲቆም ይደረጋል ፡፡

ሰ. ወንጌላውያን በሽማግሌነት አይሾሙም ፡፡

ሸ. የሽማግሌዎች ሥርዓተ ሹመት በዓመቱ መጀመሪያ ላይ በዓመታዊ ጠቅላላ የአባላት ስብሰባ ጊዜ ይሆናል ፡፡

## አንቀጽ 12. *የሽማግሌዎች ተግባር*

፩ጢሞ. 5÷1–5 , 17 ሐ.ሥራ 20÷17 , 28–35 ፩ጴጥ. 5÷1–5

ሀ. የቤተክርስቲያኒቱን የመንፈሳዊና የአስተዳደራዊ ሥራ በሳምንት አንድ ጊዜና እንደአስፈላጊነቱ እየተሰበሰቡ ከመጋቢው ጋር ሆነው ይወስናሉ፡፡

ለ. ለአማኞች የመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርትን በማስተማርና የክርስትና ሥርዓቶችን በማዘጋጀት መጋቢውና ወንጌላዊውን በመርዳት ያገለግላሉ ፡፡

ሐ. ምዕመንን በማጽናናትና በመምከር ይረዳሉ ፡ የታመሙትንና ረዳት የሌላቸውን ባልቴቶችንና ችግረኞችን ይጠይቃሉ ፡፡

መ. የጌታ እራትና የጥምቀት ሥርዓትን መጋቢውን በመርዳት ይፈጽማሉ ፡፡

ሠ. አባሎች በቤ/ክ በሥርዓት ከመጋባታቸው በፊት የመንፈሳዊ ሕይወት አቋማቸውን ከመጋቢው ጋር በመሆን ያረጋግጣሉ ፡፡

ረ. ለቤ/ክኒቱ አገልግሎት በሚቋቋሙት ልዩ ልዩ ኮሚቴዎች ውስጥ በአባልነት ወይም በመሪነት ሊገኙ ይችላሉ ፡፡

ሰ. ማናቸውም ኮሚቴ በቤተክርስቲያኒቱ መጋቢና ሽማግሌዎች ይቋቋማል ፡፡

ሸ. ከመጋቢው ጋር በመሆን ምዕመናንን ከሐሰት ትምሕርትና የመንፈስ አንድነቱን ለመጠበቅ እንዲመች በምዕመናን መካከል የሚደረጉትን ስብሰባዎች የማወቅና የመቆጣጠር ኃላፊነት አለባቸው ፡፡
እንደአስፈላጊነቱ ስብሰባውን እንዲቆም ሊያደርጉ ይችላሉ ፡፡

በ. የዓመቱን ኦዲት ኮሚቴን ይሰይማሉ ፡፡

## አንቀጽ 13 *ምክትል ሊቀመንበር*

ሀ. መጋቢው ( ሊቀመንበሩ ) ባልተገኘ ጊዜ በመጋቢው ( በሊቀመንበሩ)ምትክ ይሠራል ፡፡

ለ. በሽማግሌዎች ጉባዔ በመገኘት አብሮ ይወስናል ፡፡

ሐ. በመጋቢው ( በሊቀመንበሩ )ሲወከል የቤተክርስቲያኒተን ኦፊሲያል ደብዳቤዎች ይፈርማል ፡፡ ቤተክርስቲያኒቱ ያዘዘችውን ተግባር ይፈጽማል ፡፡

## አንቀጽ 14 *ጸሐፊ*

ሀ. የሽማግሌዎችን ቃለ ጉባዔ ይጽፋል ፡፡

ለ. በሽማግሌዎች የተወሰኑትን ውሳኔዎች አዘጋጅቶ በመጋቢው ( በሊቀመንበሩ)ወይም በምክትል ሊቀመንበሩ ፊርማ ያወጣል ፡፡

ሐ. በሽማግሌዎች ጉባዔ በመገኘት አብሮ ይወስናል ፡፡

መ. ቃለ ጉባዔውን በመዝገብ ደብዳቤዎችን በፋይል ይይዛል ፡፡

ሠ. ስብሰባዎችን ከመጋቢው ጋር በመመካከር ይጠራል ፡፡

## አንቀጽ 15 ሂሳብ ሹም

ሀ , በሽማግሌዎች እየተረዳ የዓመት በጀት ያዘጋጃል
ለ , በየሦስት ወሩ የገንዘብ ገቢና ወጪ የሚያሳይ ሂሳብ ማቅረብ
ሐ , የቤ/ክቱ ሂሳብንና ንብረትን በተመለከተ ኃላፊ ነው
መ , የቤ/ክቱን ገቢና ወጪ ሂሳብ በተገቢ መዝገብ ያሰፍራል
ሠ , የቤ/ክኒቱ ቋሚ ንብረቶች በመዝገብ ይመዘግባል

## አንቀጽ 16 አዲተር

ሀ, ከቤተክርስቲያኒቱ አስተዳደር ክፍል በሚሰጠው መመሪያ መሠረት በዓመት 1 ጊዜ ወይም እንደአስፈላጊነቱ የሂሳብ ሰነዶችና ንብረቶችን ይመረምራል ወይም ኦዲት ያደርጋል ፡፡

ሀ. በቤ/ክኒቱ ስም ለሚረከባቸው ለማናቸውም ገንዘብ ኃላፊ ነው ።

ለ.የቤ/ክኒቱን ገንዘብ በሽማግሌ ጉባዔ በተፈቀደው በጀት መሠረት ከመጋቢው ጋር በመመካከር ክፍያ ያደርጋል ።

ሐ. በየሦስት ወሩ የቤ/ክኒቱን ገንዘብ ገቢና ወጪ የሚያሳይ ዝርዝር ለሽማግሌዎች ጉባዔ ያቃርባል ።

መ. ለማንኛውም የቤ/ክኒቱ ወጪ ሕጋዊ የሆነ ደረሰኝ ያቀርባል ።

## አንቀጽ 18- ወንጌላዊ

ሀ. ከእግዚአብሔር ጥሪ ኖሮት ከቤተክርስቲያን ምስክርነት ያለው ።

ለ. ሙሉ ጊዜውን ለወንጌል አገልግሎት የሰጠና ወንጌልን ለማስተማር ችሎታ ያለው ።

ሐ. በአንዲት አጥቢያ ቤ/ክ ተቆጣጣሪነት የሚሰራ ።

መ. በየስፍራው እየተዘዘዋወረ የወንጌልን የምስራች እያሰማ አዳዲስ ነፍሳትን ወደ እግዚአብሔር መንግሥት እንዲጨመሩ የሚያስተምር ነው ።

ማቴ. 28 ÷19 ማር. 16÷15-16
ኤፌ.4÷11-13 ሐ.ሥራ 8÷5 , 8÷34-38

ሠ. ተጠሪነቱ ለመጋቢ ይሆናል ። መጋቢ በሌለ ጊዜ በቀጥታ ለሽማግሌዎች ይሆናል

ረ. በመጋቢው ወይም በሽማግሌዎች በተመደበበት የአገልግሎት ቡድኖች ግለሰቦች ጋር በመሆን ያገለግላል ። ችግረኞችን ያያል አግባብ ባለው መንገድ ሁሉ ይረዳል ።

ሰ. ከምስክርነት አገልግሎትና አገልግሎቱ ከሚመለከታቸው ክፍሎች ጋር በመሆን የወንጌል ስርጭት አገልግሎት ያስፋፋል ። አስፈላጊ በሆነ ነገር ሁሉ መጋቢውን ወይም ሽማግሌዎችን ያማክራል ። ውሳኔ የሚያስፈልገውም ከሆነ በመጋቢው በኩል ለሽማግሌዎች በማቅረብ ያስወስናል ። መጋቢ ግን ከሌለ በቀጥታ ማቅረብ ይችላል ።

ሸ. መጋቢ በሌለ ጊዜ በሽማግሌዎች ሲጋበዝ በሽማግሌዎች መደበኛ ስብሰባም ሆነ ሌሎች ስብሰባዎች ላይ ይገኛል ። ሆኖም ግን በማንኛውም ውሳኔ ላይ ድምጽ አይኖረውም

ቀ , የጌታ ዕራት , ጥምቀት , የጋብቻ ሥነ ሥርዓትና የቀብር ሥነሥርዓት ያከናውናል

## አንቀጽ 19- ዲያቆናት

## 19.1 ሥርዓተ ሹመት

ሀ. መጋቢና ሽማግሌዎች ዲያቆናትን ለአገልግሎት ሲሾሙ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን መመሪያ በመከተል መሆን አለበት ።

ሐ.ሥራ 6÷3 ፩ኛጢሞ. 3÷8–12

ለ. የዲያቆናት ቁጥር እንደአስፈላጊነቱ በሽማግሌዎች ይወሰናል ።

ሐ.ሥራ 6÷3

ሐ. የዲያቆናት የአገልግሎት ዘመን ለሁለት ዓመት ይሆናል ። ሆኖም የአገልግሎት ዘመናቸውን ሲጨርሱ ሽማግሌዎች ደግመው ሊሾሙአቸው ወይም ሊሰይሙአቸው ይችላሉ ።

መ. ዲያቆናት በሽማግሌነት የመመረጥ መብታቸው የተጠበቀ ነው ። ሆኖም ለሽምግልና እንደተመረጡ በዲቁና አገልግሎት ቦታቸው በምትኩ ሌላ ይሾማል ።

## 19.2 የዲያቆናት ተግባር

ሀ. በመንፈሳዊ አገልግሎት ሁሉ መጋቢውንና ሽማግሌዎችን ይረዳሉ ።

ለ. የቤተክርስቲያን ውሳኔዎች በስራ ላይ እንዲውሉ ያደርጋሉ ።

ሐ. የአምልኮ ሥርዓት በመልካም እንዲካሄድ ያደርጋሉ ።

መ. የምዕመናን ችግር እንዲወገድ ይረዳሉ ፡ የጉባዔው ስብሰባዎችን ያስተናግዳሉ ፡ መባን ይሰበስባሉ ፡ እንዲሁም ሌሎች የመሳሰሉትን ያከናውናሉ ።

ሠ. የቤተክርስቲያን ንብረት እንክብካቤ ያደርጋሉ ።

ሐ.ሥራ 6÷1–6 ፩ጢሞ.3÷8–13

## አንቀጽ 20

## 20.1 ኮሚቴዎች ( መሪ / ተጠሪ ) እና የአገልግሎት ክፍሎች ፡

ማቴ.9÷38 , 14÷15–21

ሀ. ማንኛውም በቤተብርስቲያኒቱ ውስጥ የሚቋቋም ኮሚቴ በመጋቢውና በሽማግሌዎች ውሳኔ ብቻ ይሆናል ።

ኮሚቴው ሲቋቋም ዋና ዓላማው ለእግዚአብ ሔር ክብር ለሰዎች ጥቅም እንደመሆኑ

ለ. ኮሚቴው ተጠሪነቱ ለመጋቢውና ለሽማግሌዎች ጉባዔ ሲሆን መሠረታዊ የሆነ መመሪያ ከእነርሱ ይቀበላል ።

ሐ. ኮሚቴው ከተሰጠው የሥራ ዝርዝርና ሥልጣን በላይ መሥራት ሲፈልግ ለመጋቢውና ለሽማግሌዎች ያስታውቃል ።

መ. ኮሚቴው ስለሥራው እንደአስፈላጊነቱ ለመጋቢውና ለሽማግሌዎች ሪፖርት ያቀርባል ።

ሠ. ኮሚቴው መጋቢውና ሽማግሌዎች ሳያውቁና ላልወከሉት ጉዳይ ከቤተክርስቲያኒቱ ውጪ ካሉ አካሎች ጋር በቀጥታ ግንኙነት ማድረግ አይፈቀድለትም ።

ረ. የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች የራሳቸው መሪ ይኖራቸዋል ።

ሰ. የተለያዩ የአገልግሎት ክፍሎች የራሳቸው መሪ ይመርጣሉ ሆኖም አስፈላጊ ሲሆን ደግሞ መጋቢውና ሽማግሌዎች ሊሰይሙ ይችላሉ ።

## 20.2 ኮሚቴዎች

ሀ. ተጠሪነታቸው ለመጋቢውና ለሽማግሌዎች ይሆናል ።

ለ. አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ የአስተዳደርና የሥነ ሥርአት ነክ ነገሮች ጉዳዩ ወደሚመለከተው የሽማግሌዎች ክፍል ያቀርባሉ ። ምንም ቢሆን በዚህ ጉዳይ ላይ አይወስኑም ።

ይህ መተዳደሪያ ደንብ እንደ አስፈላጊነቱ ሊሻሻልና እንደሁኔታውም ሊቀነስም ይችላል ።

ይህ መሠረተ ዕምነትና መተዳደሪያ ደንብ

FEBRUARY 1997 (እ . አ . አ .) ጸደቀ ።

የኢየሩሳሌም ወንጌላዊት ቤተክርስቲያን

ስቶክሆልም
ስዊድን

## ልዩ ልዩ ፕሮግራሞች

መደበኛ አምልኮ ዘወትር እሁድ ከ1600–1800
ዘወትር ሐሙስ ከ1700–1900 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናትና የትምህርት ጊዜ

ቅዳሜ በየ15 ቀን ከ1900–2400 የምሽት ጸሎት

አድራሻ
Wallingatan 3B , 6tr
111 60 Stockholm
Tel.08/208491
Fax.08/100243

JEC post giro 781954-3
JEC Cassett ministry post giro 3 84 73-5
Ethiopian Evangelical christians f.ship in Europe ) p g 3 84 79-2